በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ እና አሪዞና ሐገረ ስብከት ጽ/ቤት

The Ethiopian Orthodox Tewahdo Church Diocese of Northern California, Nevada, and Arizona Main Office

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን
ወኢ.ታምዕዕዎ ለመንፈስ ቅዱስ ዘቦቱ ዐተቡክሙ አመ ድኅንክሙ
ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ ኤፌ 4፡30

<u>ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የገጠማትን ወቅታዊ ፈተና በተመለከተ ከሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ እና አሪዞና ሐገረ ስብከት የተሰጠ መግለጫ</u>

እንደሚታወቀው ጥንታዊት ታሪካዊት እና ሐዋርያዊት የሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአስተምህሮ አንድነቷን ፣ የሥነ ምግባር እሴቷን እና የታሪክ መዝገብነቷን ጠብቃ ያቆየችው ኀቡእ የሆነው የልዑል እግዚአብሔር ጠብቆት አስተዋይ በሆኑ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቿ መሪነት በመገለጡ ነው። ለዚህም በቀዳሚነት ሊጠቀስ የሚገባው በቅዱስ ፓትርያርክ የሚመራው የቤተ ክርስቲያናችን መሪ የሆነው የሊቃነ ጳጳሳት ሕብረት ቅዱስ ሲኖዶስ ነው።

የቤተ ክርስቲያናችን የሊቃነ ጳጳሳት ኅብረት ቅዱስ ሲኖዶስ ፍጹም ጥንቃቄ የተሞላበት እና ፍጹም መንፈሳዊነት እንዲሁም አስተዋይነት የተሞላበት ሲሆን ነገር ግን በየዘመናቱ በሚነሱ የውስጥ እና የውጭ ፈተዎች ኅብረቱን ከማጠንከር ይልቅ በተለያየ ምክንያት ለማዳከም በሥራ የተጠመዱና ከኅብረቱ ዓላማ ውጪ ወይም ከሕገ ቤተ ክርስቲያን አካሄድ ውጪ የሆኑ አካላትን ድርጊት ማየት እና መስማት ለመላው የኢት/ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን ምዕመናን እና አገልጋዮች ከፍተኛ ሃዘን እና ሂደታዊ ስጋት እየሆነ ከመጣ ሰንበቷል።

በተለይም በቅርቡ ቤተ ክርስቲያን በሀገር ውስጥ እና በውጪ ሀገራት በታላቅ ድምቀት እና ደስታ አክብራ ባሳለፈችው የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ጥምቀት ማግሥት በሦሥት ሊቃነ ጳጳሳት አማካይነት የተፈጸመው ህገ ወጥ ፣ ኢ-ቀኖናዊ እና ከሲኖዶስ እውቅና ውጪ የሆነ ሹመት ለቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ፈተና ሆኖ ተነስቷል። ነገር ግን ፈተና ለቅድስት ቤ/ክርስቲያን ክብር እና ለጥንካሬዋ መሠረት ስለሆነ በታሪክ ካሳለፈቻቸው ፈተናዎች በተለየ ብቃት እና አስተዋይነት የምታልፈው መሆኑን ሀገረ ስብከታችን በጽኑእ ያምናል።

ሆኖም ግን ድርጊቱ ከህገ ቤተ ክርስቲያን እና ቤተ ክርስቲያን በቅርብ ካገኘችው የሲኖዶስ አንድነት ትሩፋት አንጻር ምንም ዓይነት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ሀገረ ስብከታችን አበክሮ እያሳወቀ መላው በሀገረ ስብከቱ ወሰን ውስጥ ባሉ አድባራት እና ገዳማት የምትገኙ ማህበረ ካህናት እና ዲያቆናት ፣ እንዲሁም መዘምራን እና ምእመናን ከብጹእ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለኃይማኖት ከሚመራው ቅዱስ ሲኖዶሳችን ስለጉዳዩ ውሳኔና መመሪያ እስኪተላለፍ ድረስ በጸሎት እና በማስተዋል እንድትጸኑ እናሳስባለን። በተጨማሪም የሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ እና አሪዞና ሀገረ ስብከት ከቅዱስ ሲኖዶስ ጎን መሆኑን እያሳወቅን ከቅዱስ ሲኖዶስ የሚወጡ ውሳኔዎችን እና መመሪያዎችን ለማስፈጸም እንደሁልጊዜውም ዝግጁ መሆናችንን ለማሳወቅ እንወዳለን።

በመጨረሻም በህገ ወጡ የሹመት አካሄድ ራሳቸውን በቀጥታ ያሳተፉ ሦሥት ሊቃነ ጳጳሳት እና ሃያ ስድስት ቆሞሳት አባቶች ድርጊታቸው ቅዱስ ሲኖዶስን ፣ መላው የሀገረ ስብከታችን አድባራት እና ገዳማት አገልጋዮችን እንዲሁም መላው የሰሜን አሜሪካ ኦርቶዶክሳውያንን ያሳዘነ መሆኑን ተረድተው ወደ ቀደመው ሲኖዶሳዊ ኅብረታቸው በይቅርታ ተመልሰው የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሲኖዶሳዊ ክብር በጠበቀ መልኩ ለቤ/ክርስቲያን ተልእኮ የድርሻቸውን እንዲወጡ ሀገረ ስብከታችን በታላቅ ትህትና ይጠይቃል።

የሰ/ካሊ/ኔቫ/አሪ ሐገረ ስብከት ጽ/ቤት
ጥር ፲፰ ፳፻፲፭ ዓ/ም

In the name of the Father, the Son, the Holy Spirit, One God, Amen

ወኢ.ታምዕዕዎ ለመንፈስ ቅዱስ ዘቦቱ ዐተቡክሙ አመ ድኅንክሙ
And do not grieve the Holy Spirit of God, in which you were sealed for the day of redemption, Eph 4:30

A statement from the Ethiopian Orthodox Tewahedo Diocese of Northern California, Nevada and Arizona regarding the current challenges facing the Holy Church.

As it is known, the ancient historical and apostolic Ethiopian Orthodox Tewahedo Church has preserved its doctrinal unity, its moral values and its historical record because of the protection of the Most High God through the guidance of its intelligent children of the Holy Spirit. For this, the Holy Synod of the Union of Bishops, which is the leader of our Church, should be mentioned first and foremost in our time.

The Holy Synod of our Church is completely careful and full of spirituality and intelligence, but instead of strengthening the union due to internal and external challenges that arise in every era, it is a dishonor for all to see and hear the actions of those who are busy with divisive work to weaken the union and are outside the purpose of the union or outside the way of the constitutional church. As a result, the EOTC Christian parishioners and servants have been facing to great sadness and procedural risk through time.

In particular, the illegal, non-canonical and synodically unrecognized appointment by three bishops on the day after the feast of epiphany-baptism of our Savior Jesus Christ, which the church recently celebrated with great solemnity and joy at home and abroad, has become a great challenge and risk for the church. However, our Diocese firmly believes that such challenges are the basis of its honor and strength of the Holy Church; and that it will pass it with competence and intelligence unlike the challenges it has passed through in history.

However, our Diocese emphasizes that this act is not acceptable in view of the legacy of the Synod of the Church, Canonical procedures, and the Synod unity which the Church has recently acquired. We urge all the EOTC priests and deacons, as well as choirs and laity in the parishes and monasteries within the boundaries of the Diocese, to persevere your prayer and Orthodoxy calmness until the resolution of the issue is passed from our Holy Synod led by His Holiness Abune Matthias I, the Patriarch of Ethiopia, Archbishop Zeaxum we'ich'egē zemenibere tekilehayimanot. In addition, we would like to inform you that the Diocese of EOTC Northern California, Nevada and Arizona is on the side of the Holy Synod and that we are always ready to implement the decisions and directives issued by the Holy Synod.

Finally, the three bishops and twenty-six monks who were directly involved in the illegal appointment, non-canonical and synodically unrecognized procedure shall know that their action caused a great sorrow to all the ministers of our diocese and monasteries as well as the entire North American EOTC community. Thus, our Diocese humbly asks those fathers to regret their action and return to their previous synodal association with forgiveness and do their part for the mission of the church in a way that preserves the synodal honor of the Holy EOTC Church.

Jan 26, 2023
EOTC NCa, NV AZ Diocese